# የ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል በጀት መረጃ ለዜጎች የተዘጋጀ



**ገንዘብ ሚኒስቴር**

**አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ**

# በዉስጥ ገጽ


መልዕክት.................................................................................i

ምስጋና.................................................................................iii

መግቢያ.................................................................................1

ስለመንግስት በጀት ...................................................................2

ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕይታ ......................................................7

የመንግስት በጀት ምንጩ ከየት ነዉ? ................................................7

የመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎችና የወጪ አደራረግ፤ (የዓመቱ በጀት በምን ላይ ይዉላል?)........................................................................8

የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሓረጎች መግለጫ፤.........................11

# መልዕክት

የኢትዮጵያ መንግስት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁናቴዎች ላይ በመመስረትና ስራ ላይ የዋሉ የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎችን በመከተል የኢኮኖሚ እድገቱን ለማፋጠን በቁርጠኝነት እየሰራ የሚገኝ ሲሆን፤ የሀገሪቱ ፊስካል ፖሊስም በትምህርት ላይ ከፍተኛ ኢንቨስት በማድረግ ድህነትን ለመቀነስ እና የህዝባችንን ደህንነት ለማሻሻል፤ የዜጎችን አቅም በመፍጠር መሠረታዊ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን በማሳደግ ፣ መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት፣ የስራ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ተቋማትን በመገንባት እና ባልተማከለ አስተዳደርን መልካም አስተዳደርን ለመጎልበት እየሰራ ይገኛል። ይኸዉ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋገጥ፣ የድህነት ተኮር ስራዎች ዉጤታማነትና የተደረጉ መዋቅራዊ ማሻሻያዎች ላለፉት አስርት ዓመታት ለተገኘው አስደናቂ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የተመዘገበዉን የኢኮኖሚ ዕድገት ሳይዋዥቅ በቀጣይነት እዉን ለማድረግና በአሁኑ ጊዜም ሀገሪቱን የማክሮ አኮኖሚ በዘላቂነት ለማረጋገት የተወጠነዉን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳዎችን (የማክሮ ኢኮኖሚ ፣ የመዋቅራዊና የዘርፍ ማሻሻያዎች) እውን ለማድረግ መንግስት በሁሉም ደረጃ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የዜጎች ተሳትፎንና ግልጽነትን በመተግበር የተያቂነት ስርዓቱ እንዲሰፍን በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል። ለዚህም ማረጋገጫ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ሪፎርም አንድ አካል የሆነዉን የፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓት ትግበራ ላለፉት ዓመታት በሁሉም መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ ተፈጻሚ በማድረግ ማህበረሰቡ የታቀደውን ወጪና አፈጻጸሙን በቀላሉ በመከታተልና በተመዘጋቡ ውጤቶች ላይም የተጠያቂነት ስርዓቱ ገብር እንዲሆን በመታገሉ መልካም ዉጤት ሊመዘገብ ችሏል።

ይህንኑ የግልጽነትና ሁለንተናዊ የዜጎች ተሳትፎን በመጠናከር በመንግስት በጀት አፈጻጸም ላይ የተጠያቂነት ስርዓቱ ተፈጻሚነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የገንዘብ ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ ለ2014

በጀት ዓመት የጸደቀዉ በጀት መሰረት በማድረግ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ በቀላሉ ተረድቶት በትግበሩ ሂደቱ ላይ በሙሉ አቅሙ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ አዘጋጅቶ አሰራጭቷል፡፡ በጀቱም የ10 (አስር) ዓመት ብሔራዊው የልማት ዕቅድ እንዲሁም ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳዎችን በመተግበርና መነቆዎችን ለዜጎች ሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለድህነት ቅነሳና አጠቃላይ አካታች ዕድገትን ለማምጣት ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡

ስለሆነም ይህ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ በሀገሪቱ ህግ-አዉጪዉ በተፈቀደው የመንግስት የገቢና የወጪ ዕቅዶች ውስጥ የተካተተውን በጀት ማህበረሰቡ በቀላሉ ተረድቶና ተጠቅሞ በመንግስት የልማት ስራዎች ላይ ተሳትፎዉን በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓት ማስፈን እንዲቻል ሚናቸዉን እንድወጣ ጥሪዬን ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር

## ምስጋና

ይህ ለዜጎች የተዘጋጀዉን የ2014 በጀት መረጃ ሰነድ በገንዘብ ሚኒስቴር በተቋቋመ ቡድን ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፤ ለሰነዱ ዝግጅት ድጋፍና በወቅቱ ጸድቆ እንዲሰራጭ ላደረጉት ለመንግስት ፋይናንስና ፊስካል ፖሊሲ ዘርፍ፤ ለመንግስት ወጪ አስተዳደር ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ሰነዱን አዘጋጅተዉ ለቀረቡት የቡድኑ አባላት ምስጋናችን ያላቀ ነዉ።

## 1. መግቢያ

ሀገራዊ የበጀት ስርዓቱ መንግስት በፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት የሚከናወኑ ተግባራትንና የማስፈጸሚያ ሀብትን አመጣጥኖ የሚያቅድበት ነዉ፡፡ በዚህም የመንግስት በጀት የሚያመለክተዉ መንግስት በበጀት ዓመቱ የሚሰበስበዉን ቀረጥና ሌሎች ገቢዎች፣ ለዜጎች የሚቀርቡ አገልግሎቶችንና የፋይናንስ ጉድለቶችን ማሟላት የሚያስችል የብድር ዕዳ በመወሰን የኢኮኖሚ ዕድገቱን ማፍጠንን፣ ተጨማሪ የስራ ዕድሎችን የሚፈጥርበት፣ የመሰረተ ልማቱን የሚያስፋፋበትና ድህነትንና ኢፍትሓዊነትን የሚያጠፋበት ሂደት ሲሆን፤ እነዚህን ዉሳኔዎች ተፈጻሚ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ እንዲዉል የተፈቀደዉን በጀት ለሁሉም ሊገባ በሚችል መልኩ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን በማዘጋጀናት ተደራሽ በማድረግ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ አድርጓል፡፡

## የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ስንል ምን ማለታችን ነዉ?

ይህ በገንዘብ ሚንስቴር ተዘጋጅቶ ለዜጎች የሚቀርበዉ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ የመንግስት በጀት ሂደት ማለትም የበጀት ዝግጅትን፣ በጀትን ማጽደቅ፣ በጀትን ስራ ላይ ማዋልንና ስራ ላይ የዋለን በጀት እንዴት እንደሚገመገም እንዲሁም በእያንዳንዱ ሂደት ሃላፊነት የተሰጠዉ አካልና የስራ ድርሻ ምን እንደሆነና ዜጎችም በዚህ የበጀት ሂደት እንዴትና መቼ መሳተፍ እንዳለባቸዉ በጥቅል በማመልከት በ2014 በጀት ዓመት የዜጎችን ቅድመ-ፍላጎቶች እና የመንግስት የተኩረት አቅጣጫ መሰረት የተመደባዉን በጀትና በበጀቱ የሚከናወኑ አንኳር ጉዳዮችን ለሀገሪቱ ዜጎች የሚያስረዳ ነዉ፡፡

## መንግስት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን ለምን ያዘጋጃል?

ይህ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ስለመንግስት በጀት ሂደት አጠቃላይ ግንዛቤን በማህበረሰቡ ላይ በመፍጠርና የመረጃ ተደራሽነት በማሳደግ በመንግስት በሚከናወኑ የልማት ስራዎች ላይ ተሳትፍና ጠያቂ ማህበረሰብ እንዲሆን አቅም ለመፍጠር ሲሆን፤ መንግስትም የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል

ከህዝብ በሰበሰበዉ ሀብት ምን እንደሚሰራና እንዴት ስራ ላይ እንደሚያዉል የሚገልጽበት ሰነድ ነዉ።

## 2. ስለመንግስት በጀት

### የመንግስት በጀት ስንል ምን ማለታችን ነዉ?

የመንግስት በጀት በአንድ የበጀት ዓመት ስለ መንግስት ገቢና ወጪ የሚተነበይበት ሰነድ ሆኖ ሁሉም የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከተሰጣቸዉ ተግበርና ሃላፊነት አንጻር ሊያሳኩ ያስቀመጡትን ዓለማ እንዴትና በምን ያህል ሀብት እንደሚያከናዉኑ የሚያሳይ ሰነድ ነዉ። የበጀት ሰነዱም በሀገሪቱ ህግ-አዉጭ አካል ከጸደቀ በኋላ ስራ ላይ የሚዉል ህጋዊ ሰነድ ይሆናል።

### መንግስት በጀትን ለምን ያዘጋጃል?

መንግስት የዜጎችን ፍላጎት ሁሉ በአንድ ጊዜ ለማሟት የሀብት ዉስንነት ስላለበት ለዜጎች በቅድሚያ መቅረብ ያለባቸዉን አገልግሎቶች በመለየትና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሀብት ከየትና እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ለመወስን በጀት ያዘጋጃል። በመሆኑም በበጀት ዝግጅት ቅድሚያ የተሰጣቸዉና በበጀት የተደገፉ ተግባራት የመንግስትን ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን የሚጠቁሙ ይሆናል ማለት ነዉ።

## የበጀት ሂደት

የኢትዮጵ መንግስት የበጀት ሂደት ከማዕከላዊ መንግስት እስከ ታችኛዉ አስተዳደራዊ የስልጣንን እርከን ድረስ በተመሳሳይ አራት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፤ እነዚህ የበጀት ሂደቶች የገንዘብ ሚ/ር ባወጣዉ የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በሁሉም ባለበጀት መ/ቤቶች ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸዉ፡ ፡

አራቱ የመንግስት በጀት ሂደቶች፡-

1) በጀትን ማዘጋጀት (ማርቀቅና ቅርጽ ማስያዝ)፤

2) የተዘጋጀን በጀት ማጽደቅ (በህግ አዉጭዉ የሚከናወን)፤

3) በጀትን መተግበር( በጀትን ስራ ላይ የማዋል ሂደት) እና

4) የበጀት ቁጥጥር ( የበጀት አፈጻጸምን መገምገም፤ ኦዲት ማድረግና መከታተል) ናቸዉ፡፡

በፋይናንስ ካለንደሩ መመሪያ መሰረት በጀትን ለማዘጋጀት፣ ለማጸደቅ፤ ስራ ላይ ለማዋልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የጊዜ ሰለዳ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

| **የበጀት ሂደቶች** | **በእያንዳንዱ የበጀት ሂደት የሚከናወኑ እንኳር ተግባራት** | **ትግባራቱን ለመፈጸም ኃላፊነት የተሰጠዉ አካል** | **የትግበራ ጊዜ** |
|---|---|---|---|
| **የበጀት ዝግጅት** | ▪ የማክሮ-ኢኮኖሚና የፊሲካል ማእቀፍ ዝግጅት | ገንዘብ ሚኒስቴር | እስከ ህዳር 01 የሚጠናቀቅ |
| | ▪ በተዘጋጀዉ የማክሮ-ኢኮኖሚና የፊሲካል ማእቀፍ መነሻነት አመታዊ የፊሲካል እቅድ ማዘጋጀት | ገንዘብ ሚኒስቴር | እስከ ጥር 17 የሚጠናቀቅ |
| | ▪ መንግስታዊ የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ማዘጋጀት፤ አመታዊ ለክልል መንግስታት የሚሰጠዉን ድጎማ በጀት ግምት ማዘጋት እና የበጀት ጥሪ ለባለበጀት መ/ቤቶች ማድረግ፤ | ገንዘብ ሚኒስቴር | እስከ የካቲት 01 የሚጠናቀቅ |
| | ▪ ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ጥያቄ ያቀርባሉ፤ | ባለበጀት መ/ቤቶች | እስከ መጋቢት 15 የሚጠናቀቅ |
| | ▪ በጀት ሰሚ ጉባኤ ማድረግ፤ | ገንዘብ ሚ/ር እና | እስከ ግንቦት 17 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ባለበጀት መ/ቤቶች | የሚጠናቀቅ |
| | ▪ ተደግፎ የቀረበዉን አመታዊ በጀት ላይ መወሰን፤ | የመንግስት አስፈጻሚ አካላት (የሚኒስትሮች ምክር ቤት/ካብኔ) | እስከ ሰኔ 23 የሚጠናቀቅ |
| **በጀትን ማጽደቅ** | ▪ የቀረበዉን ረቂቅ በጀት ማጽደቅና መመደብ | ህግ አዉጭ አካላት (የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት)፤ | እስከ ሰኔ 30 የሚጠናቀቅ |
| **በጀትን መተግበር** | ▪ በጀትን መተግበር/ ስራ ላይ ማዋል፤ | በጀት የተመደበላቸዉ ባለ በጀት መ/ቤቶች | ከሃምሌ 1 እሰከ ሰኔ 30 |
| **የበጀት ቁጥጥር** | ▪ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፤<br>▪ የባለበጀት መ/ቤቶችን ሂሳብ መመርመር፤<br>▪ የአፈጻጸም ግድፈቶችንና ስህተቶችን መለየት፤ | ገንዘብ ሚ/ር፣ ባለበጀት መ/ቤቶች፣ የፌደራሉ ኦዲት መ/ቤትና የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት፤ | ከሃምሌ 1 እሰከ ሰኔ 30 |

## በበጀት ሂደቶች ዜጎች እንዴት ይሳተፋሉ?


የኢትዮጵያ ህገ-መንግሰት ዜጎች በመንግስት ሁለንተናዊ ተግባራት በሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይደግፋል፡፡ ለአብነትም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 6 እንደተጠቀሰዉ መንግሰት ዜጎችን በብሄራዊ ልማት ፖሊሲና ፕሮግራም ዝግጅት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁሌም ሊያበረታቱ ይገባል፤ መንግስት የዜጎችን በልማት የመነሳሳት ጥረታቸዉን ሁሌም ሊያግዛቸዉ ሃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ስለዚህም በህገ-መንግሰቱ በተደነገገዉ መሰረት ዜጎች በመንግስት የበጀት ሂደቶች መሳተፍ የሚያስችላቸዉ  አማራጮች ሁሉ  መሳተፍ ስለሚችሉ  በመንግስት ተግባራት ላይ ተሰሚነት እንዲኖራቸዉ በማበረታታት፤ በየደረጃዉ ባለዉ አስተዳደራዊ እርከን ላይ ዜጎችን የሚመለከቱ ብሄራዊ የልማት ፍላጎቶችና ጉድለቶች ላይ መንግስትን እንዲሞግቱ፤ በጋራ እንዲሰሩ፤ እንዲወስኑና እንዲያሻሽሉ ይጠበቃል፡፡

## ዜጎች በሚከተሉት ስልጦችና ሂደቶች ማሳተፍ ይችላሉ፤



### በተወካዮቹ አማካኝነት

የህግ አዉጪዉ/የህዝብ ተመራጮች  አስፈጻሚዉን አካል በእቅድ ያቀረበዉን የወጪና   የገቢ አሰባሰብ እንዲሁም እቅዱን ለማስፈጸም በሰጠዉ ዉሳኔና የተገኘዉን ዉጤት መነሻ በማድረግ በጥልቀት ሊመረምርና ሃላፊነቱን ባልተወጣ ጊዜ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡



### ቅድመ-በጀት መግለጫ

-የቅድመ በጀት መግለጫ- ህዝቡ የመንግሰትን የወጪና የገቢ እቀድ እንዲያዉቅ በማድረግ የበጀት አመቱ በጀት ከመጽደቁ በፊት ለበጀት አፈጻጸም ዉጤታማነት ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ከህዘቡ እንዲያገኝ እድል ይሰጣል፤

-የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአስፈጻሚ አካላት የቀረበለትን በጀት ከማጽደቁ በፊት የሲቢክ ማህበራት፤ ግለሰቦች፤ ተቋማትና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላት በቀረበዉ ረቂቅ በጀት ላይ ሀሳብና አስተያየት እዲያቀርቡ በሚደረግ ሂደት ዜጎች መሳተፍ ይችላሉ፤



### በመንግስት ተቋማት የህዝብ ተሳትፎ መድረኮች

የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ከህብረተሰቡና  ከሚመለከታቸዉ  ባለድርሻ አካላት ጋር በተቋማቸዉ የሩብ አመትና አመታዊ የበጀትና እቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ዜጎች መሳተፍ ይችልሉ፤



### ማህበረሰብ አቀፍ የልማት ኮሚቴዎች

በመንግስት አስፈጻሚ አካለትና በማህበረሰቡ ተነሳሽነት በተመረጡና በተቋቋሙ የልማት ኮሚቴዎች አማካኝነት  ዜጎች ተሳታፊ ይሆናሉ፤



### ሁለንተናዊ የዜጎች ተሳትፎ ስልቶች

**የግልጽነትና የማህበራዊ ተጠያቂነት ስርዓትን በህብረተሰቡ ዘንድ ለማስረጽና ለማጠናከር የተለያዩ ስልቶችን ተግባራዊ ይደረጋሉ፤**

**-የዜጎች ቅድመ በጀት ዉይይት ስልት፡-** ዜጎች በወረዳዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ በማድረግ በበጀት ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ የሚገባቸዉን ፍላጎቶችን ይለያሉ፤

**-የማህበራዊ ተጠያቂነት ስልቶች፡-** የማህበረሰቡን አቅም በማሳደግ የመሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፤

## 3. ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ዳሰሳ


የማክሮ ኢኮኖሚና ፊሲካል ማእቀፍ ማለት የመካከለኛ ጊዜ( ከሶስት እስከ አምስት አመት ) ተንከባላይ የወጪና የገቢ እቅድ ሲሆን በየአመቱ የሚዘጋጅና በሚኒስተሮች ም/ቤት የሚጸድቅ ሰነድ ሲሆን፤ በማዕቀፉም የፋይናንስ ሀብት (መደበኛ ገቢ፣ ብድርና ድጋፍ)፣ ጠቅላላ አገራዊ ገቢና ወጪ፣ የፌዴራሉንና የክልል መንግስታት ወጪ፤ የተከታታይ አምስት አመታት የስራ ማስከጃና የካፒታል ወጪ መረጃዎችን አካቶ የያዘ ነዉ። በተጨማሪም የፌዴራሉ መንግስት ለክልል መንግስታት የሚያደርገዉን የበጀት ድጎማና የበጀት ጉድለቱንና ጉድለቱ እንዴት እንደሚሸፈን ጭምር የሚያሳይ ነዉ።

በመሆኑም በ2013 በጀት ዓመት  የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ  በ8.5 በመቶ እንደሚያድግ የሚጠበቅ ቢሆንም በኮቪድ-19 ወረርሽኝና በሀገርቱ በነበሩ ያለመረጋጋቶች ምክንያት የተጠበቀዉን ያህል ላይሆን ይችላል። በሌላ በኩል በመጋቢት ወር 2013 ዓ.ም የተመዘገበው የ12 ወራት አማካይ አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ዕድገት 20.2 በመቶ ሲሆን፤ ለዚህ ንረት ምንጩ በዋናነት ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ናቸዉ።

## 4. የመንግስት በጀት ምንጩ ከየት ነዉ?

የኢትዮጵያ መንግስት በ2014 በጀት ዓመት ሊፈጽማቸዉ ያቀዳቸዉን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ብር 561.67 ቢሊዮን የበጀተ ሲሆን፤ ይህም በ2013 በጀት ዓመት ከተበጀተዉ ብር 476.01 ቢሊዮን የብር 85.66 ቢሊዮን (18 በመቶ) ብልጫ አለዉ።

መንግስት የመደበዉ አጠቃላይ አገራዊ በጀቱ ከሚከተሉት የበጀት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-




የበጀት አመቱ የመንግስት የበጀት ጉድለት 2.67 መቶኛ ከአጠቃላዩ አገራዊ የኢኮኖሚ ምርት ዕድገት ሲሆን፤ ይህንን የበጀት ጉድለት ከመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ድጋፍ፤ ከዉጪ የፕሮጄክት ብድርና ከአገር ዉስጥ ብድር የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 5. የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ እና የወጪ አደራረግ

### በወጪ አደራረግ የመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች

የመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች የዜጎች ቅድመ ፍላጎቶች ሆነዉ ነባራዊዉና የቀጣይ ማክሮ-ኢኮኖሚ ትንበያዎች፤ የሀገሪቱ የአስር ዓመት ብሄራዊ ዕቅድ እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ለዜጎች የስራ እድል ለመፍጥር፤ ድህነት ቅነሳና ሁሉን አካታች ሀገራዊ እድገት ለማምጣት ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘዉን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳን (የማክሮ ኢኮኖሚ፣ መዋቅራና ተቋማዊ ለዉጦች) መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የበጀት ምደባዉ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ትግበራ ሂደት ያጋጠሙትን ተግዳሮቶችንም ለመቅረፍ ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡

### መንግስት የሰበሰበዉን ገቢ በምን ላይ ያዉላል?


አጠቃላይ ለዚህ በጀት ዓመት የተመደበዉ ሀብት በሚከተሉት ዋና ዋና የወጪ ዓይነቶች ተከፋፍሏል፡-

**የመንግስት ወጪ አደራረግ በዋና ዋና ወጪ ዓይነቶች (በቢሊዮን ብር)**

| የወጪ ዓይነቶች | በ2013 በጀት ዓመት | በ2014 በጀት ዓመት | ልዩነት |
|---|---|---|---|
| ለመደበኛ ወጪ | 133.32 | 162.17 | 28.85 |
| ለካፒታል ወጪ | 160.33 | 183.55 | 23.22 |
| ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ | 176.36 | 203.95 | 27.59 |
| ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ | 6 | 12 | 6 |
| ድምር | 476.01 | 561.67 | 85.7 |

**በ2014 በጀት ዓመት ለዋና ዋና ፕሮጀክቶች የተመደበ የካፒታል በጀት**

**በቢሊዮን ብር**


70
60
50
40
30
20
10
0
26.9
16.4
0.5
3.74
18
66.6
2.21
1.2
15.79
5.09
ለትምህርት ዘርፍ ልማት ቴክኒክና ሙያን ጨምሮ
ለከተማና ገጠር ልማታዊ ሴፍትኔት የሥራ ዕድል…
በግብርና ዘርፍ የተቀናጀ ኣነስተኛ የመስኖ ልማት…
የመጠጥ ዉሃና ስኒቴሽን
የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት
ለመንገድ ግንበታና ማሻሻያ
ለመንግሥት ቢሮዎች እና መኖሪያ ቤቶች ግንበታ…
ለትግራይ መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት
ለጤና ሴክተር ልማት
የከተሞች መሰረተ ልማት ማስፋፊያ

## 6. የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሓረጎች መግለጫ

1) **<u>የአስተዳደር ስልጣን:-</u>** በመንግስት አስተዳደር ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ያለው የስልጣን ተዋረድ ማለት ነዉ፡፡

2) **<u>የበጀት ጥሪ፡-</u>** በገንዘብ ሚኒስቴር የተዘጋጀና ባለበጀት መ/ቤቶችም በተቀመጠዉ የበጀት ማዘጋጃ መመሪያ መሰረት ለመ/ቤታቸዉ እቅድ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጋቸዉን በጀት አዘጋጅተዉ እንዲቀርቡ ማሳሰብ፡፡

3) **<u>የበጀት ጉድለት፡-</u>** በበጀት ዓመቱ በወጪና ገቢ በጀት መካከል ያለ ልዩነት ሲሆን፤ መጠኑም ከጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር በመቶኛ የመቀመጥ ነዉ፡፡

4) **<u>የበጀት ጥያቄ፡-</u>** የመንግስት ተቋማጽ ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላለፋቸዉ የበጀት ጥሪ መሰረት ያስፈልገኛል ያለዉን የበጀት አመቱን የወጪ አይነት በዝርዝር ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚያቀርበዉ ጥያቄ ነዉ፡፡

5) **<u>የበጀት ድጎማ፡-</u>** የፌዴራሉ መንግስት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ ነው፡፡

6) **<u>የካፒታል ወጪ፡-</u>** በተቋማት የመንግሰትን አገልግሎት ለመስጠትና ለማሻሻል ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይንም ለማሻሻል የሚዉል ወጪ ነዉ፡፡

7) **<u>የዜጎች በጀት፡-</u>** መሠረታዊ የበጀት መረጃዎች ዜጎች ሊረዱት በሚችሉ ቀላል እና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ተደራሽ የሚደረግ የበጀት መረጃ ሰነድ ነው፡፡

8) **<u>የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ፡-</u>** ከመንግስት የሚሰጡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ለማሻሻል ዜጎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና የአፈፃፀም ግምገማ ላይ የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ተሳትፎን ያመለክታል፡፡

9) **<u>የሀገር ውስጥ በጀት ምንጭ፡-</u>** መንግስት የበጀት ዓመቱን ወጪ ለመሸፈን ከሀገር ዉስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበስበዉ እንዲሁም ከሀገር ዉስጥ የሚያገኘዉን ብድር የሚያመለክት ነዉ፡፡

10) **<u>የኢኮኖሚ መረጋጋት፡-</u>** የማክሮ ኢኮኖሚው ከመጠን በላይ አለመለዋወጥና በተከታታይነት የማያቋርጥ የዕድገት መጠን፣ ዝቅተኛ እና የተረጋጋ የዋጋ ግሽበት ያለው ኢኮኖሚ ማለት ነዉ።

11) **<u>የውጭ እርዳታ፡-</u>** በመንግስት አቅም ሊሸፈኑ የማይችሉትን መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለመደገፍና ለማገዝ ከሚፈልጉ የዉጭ መንግስታትና እርዳታ ድርጅቶች የሚገኝ ሀብትን ያጠቃልላል፡፡

12) **<u>የኢትዮጵያ በጀት ዓመት፡-</u>** በኢትዮጲያ ዘመን አቆጣጠር መሰረት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ያለዉ አመታዊ የበጀት ትግበራ ጊዜ ማለት ነው።

13) **<u>የውጭ ብድር፡-</u>** መንግስት የወጪ ግዴታዉን ለመወጣት የሚያስፈልገዉን ሀብት ከሀገር ዉስጥ ከሚገኝ የበጀት ምንጭ መሸፈን በማይችልበት ሁኔታ የበጀት ጉድለቱን ለማሟላት ከዉጭ አበዳሪዎች የሚገኘዉን ሀብት ነዉ፡፡

14) **<u>የፊስካል ፖሊሲ፡-</u>** መንግስት ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወጪ አደረራረግ የሚመራበት ስርዓት ነው።

15) **የፋይናንስ ሀብት/ገቢ፡-** መንግስት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚዉሉ ወጪዎችን ለመሸፈን ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚገኘዉ ገንዘብ ማለት ነው።

16) **<u>የመካከለኛ ጊዜ የወጪ ማዕቀፍ፡-</u>** የኢትዮጵያ መንግስት የሦስት ዓመት የወጪ ዕቅዶችን ያወጣል፡ በጀቶች የመንግስትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሚያንፀባርቁ እና ለመንግስት መልሶ ግንባታ እና ልማት ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው።

17) **<u>ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት፡-</u>** በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ በአንድ ሀገር ውስጥ የተደረጉ ከሁሉም ከተጠናቀቁ ምርትና አገልግሎቶች የተገኘ የገንዘብ ዋጋ ነው።

18)**<u>የዋጋ ግሽበት/ንረት መጠን፡-</u>** አሁን ያለዉን የሸቀጦትና አገልግሎቶች ዋጋ ከዚህ በፊት ከነበረው ዋጋ ጋር በማነጻጸር የዋጋ ለውጡን በመቶኛ መስቀመጥ ነዉ፡፡

19)**<u>ማክሮ ኢኮኖሚ፡-</u>** የአጠቃላይ ወይም ጥቅል ሀገራዊ ኢኮኖሚዉ አወቃቀር፣ አፈፃፀም፣ ባህሪንና የውሳኔ አሰጣጡን የሚያመለክት ነው፡፡

20)**<u>የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ፡-</u>** አመታዊ የፊዝካል ዕቅዶችና ግቦች የፖሊሲ ትግበራ አማራጮች የሚወሰኑበት እንዲሁም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የበጀት ዓመቱ የገቢና ወጪ ግምት የሚከናወንበት ማዕቀፍ ነዉ፡፡

21)**<u>ሞኒተሪ ፖሊሲ፡-</u>** አጠቃላይ የገንዘብ አቅርቦትን በመቆጣጠር ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖር ለማድረግ የሀገሪቱ ብሄራዊ ባንክ የሚያወጣዉና የሚተገብረዉ ስርዓት ነው፡፡

22)**<u>ፖሊሲ፡-</u>** በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውና ሊተገሩ የታቀዱ ውጥኖች ማስፈፈፀሚያ መመሪያ ነው፡፡

23)**<u>ቅድመ-በጀት ውይይት፡-</u>** በወረዳ ደረጃ የዜጎችን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ቅድመ-ፍላጎቶችና ምርጫዎች በዕቀድ ለማካተትና ለማከናወን ከወረዳዉ ማህበረስበ ክፍሎች ጋር የሚደረግ ዉይይት ነዉ፡፡

24)**<u>ቅድመ-በጀት መግለጫ፡-</u>** በመንግሰት አስፈጻሚ አካላት የቀረበዉን የበጀት ዓመቱ የበጀት ፕሮፖዛል ከመጽደቁ በፊት የህግ አዉጪዉ አካል በቀረበዉ ላይ ዉይይትና ክርክር የሚያድርግበት እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸዉ የማህበረሰብ ተወካዮች፣ ተቋማትና ግለሰቦች አስተያየት ሰተዉ ማስተካከያ የተደረገበት መግለጫ ነዉ፡፡

25)**<u>የመንግስት ተቋማት (የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች)፡-</u>** ማንኛዉንም የፌዴራል መ/ቤት በአዋጅ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል ከመንግስት በሚመደብላቸው በጀት የሚተዳደሩና የፋይናንስ እንቅስቃሴያቸዉ በመንግስት ቁጥጥር የሚደረግባቸዉን ያካትታል፡፡

26)**<u>መደበኛ በጀት (የስራ ማስኬጃ ወጪ)፡-</u>** ቋሚ ንብረቶችን ለመፍጠር የማይዉልና መንግስታዊ ስራዎች ለማከናወን ለሚያስፈልጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ብቻ የሚያስፈልግ ወጪ ነዉ፡፡

27)**<u>ተንከበላይ ወጪ፡-</u>** ከአንዱ በጀት ዓመት ወደሚቀጥለዉ የሚከባለልና በየጊዜዉ የሚተደስ ወጪን ያመለክታል፡፡

28)**<u>ዘላቂ የልማት ግቦች፡-</u>** ለሁሉም የተሻለ እና ቀጣይነት ያለው ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶች ማለትም ድህነትን፣ ኢ-ፍትሃዊነትን፣ የአየር ንብረት ለውጥንና የአካባቢ መበላሸትን ለመቅረፍ እንዲሁም ሰላምን ለማስፈን የተወጠኑ ግቦች ናቸዉ፡፡